# ቅርቅሀ-ነሽ አሉ

የማሌሊት ዝላይ
እንዷል ያያሽ ሁሉ
ምድር አይብቃኝ ባይ
ቅርቅሀ ነሽ-አሉ።

ነሽ አሉ ቅርቅሀ
የበረሃ ሽመል
በራሱ ዕሳት ሰብቆ
በራሱ ዕሚቃጠል።

ሽመል ዘነዘና
ቅርቅሀ ነሽ አሉ
ለገጀራው ያጨሽ
ቤተ-ሰሪው ሁሉ።

እንደዕባብ ተሳቢ ሰርሽ
እንደ ሰርዶ
ድንበር ገፊ አመልሽ
ጎረቤት ተራምዶ
በሰዎች መሬት ላይ
ባለርስት ያረገሽ
ነሽ አሉ ቅርቅሀ
ህዝብ አዳም ያወቀሽ።

ግና ግና ድንገት
ድርቅ ሆኖ ግንቦት
ሰማዩ ዕምባው ደርቆ
ዕለቅሶዉን ሲያቆም
ያንቺም ቀንሽ አልቆ
የትም ይሁን የትም
ሲጠፉ ጨርሶ ዕርጥበት ካፈሩ
ደልቶት ተዘባኖ
መኖር እንዳማሩ
የህልም ዛት ሆኖ
ሲነፍስ አየሩ
ዘርሽን ሳያጠፋው
መቀመቅ ሰንቆ
ሞትሽን አሳምሪው
ቀን ሳይሄድ ዕርቆ!!

________/__________

መጋቢት 1999
አብርሃም በየነ (ከአትላንታ)